የሃገር ተቆጣጣሪና የሕዝብ
አቤቱታ ሰሚ ተቋም

# የሕዝብ አቤቱታ ሰሚ ተቋም



የሃገር ተቆጣጣሪ የሕዝብ አቤቱታ ሰሚ
ተቋም ጭምር በመሆኑ ይህን ተግባሩን በየሕዝብ
አቤቱታ ሰሚ ተቋም በኩል ያከናውናል

## አቤቱታ ማቅረብ የሚችለው ማነው?

ማንኛውም ሰው፣ በየትኛውም ዕድሜ ላይ የሚገኝ



## አቤቱታ የሚቀርበው በምን ላይ ነው?

**ስለተፈጸመ ወይም ስላልተፈጸመ ድርጊት**

አቤቱታ አቅራቢውን የሚጎዳ

ወይም

የሚገባውን ጥቅማ ጥቅም ከማግኘት የሚከለክለው ከሆነ

**የተፈጸመው ወይም ያልተፈጸመው ድርጊት**

ከሕግ የሚቃረን ከሆነ

ወይም

ሕጋዊ ስልጣን ሳይኖረው ከሆነ

ወይም

ከመልካም አስተዳደር ጋር የሚቃረን ከሆነ

ወይም

ከፍተኛ የሆነ ከሁኔታ ጋር ያለመቀያየር ወይም ኢ-ፍትሐዊነትን በግልጽ የሚያንጸባርቅ ከሆነ ነው

## ከአቤቱታው ጋር ተያይዞ መቅረብ ያለበት ምንድን ነው?

- የመገናኛ ዝርዝር (ስልክ፣ ኢሜይል አድራሻ፣ ወዘተ...)
- በቀረበው አቤቱታ ላይ አቤቱታ ለቀረበበት አካል የተላከ መልእክት
- አቤቱታ ከቀረበበት አካል የተሰጡ ምላሾች
- ሌሎች አግባብነት ያላቸው ሰነዶች



## አቤቱታ የሚቀርበው በማን ላይ ነው?

- የመንግስት ሚኒስቴር መ/ቤቶች
- የአካባቢ ባለስልጣን መ/ቤቶች
- የመንግስት ድርጅቶችና ተቋማት
- የመንግስት ኩባንያዎች
- ሌሎች በሕግ የተገለጹ የሕዝብ ተቋማት

## ምርመራ የማይደረግባቸው አቤቱታዎች የትኞቹ ናቸው?

- የግል ተቋማትና ግለሰቦች ላይ የሚቀርቡ አቤቱታዎች
- የሃገሪቱን ፕሬዚዳንት ወይም ፓርላማ የመሳሰሉ የመንግስት አካላት ላይ የሚቀርብ አቤቱታ
- የፍትሕ አካል ወይም የፍትሕን ስራ የሚሰራ አካል ላይ የሚቀርብ አቤቱታ
- በፍ/ቤት በመታየት ላይ ባለ ጉዳይ ወይም ፍ/ቤት በወሰነው ጉዳይ ላይ የሚቀርብ አቤቱታ
- በእስራኤል የጦር ሃይል መደበኛ ሰራዊት ወይም ተጠባባቂ ሃይል ወይም በፖሊስ ሰራዊት ወይም በእስር ቤት ጥበቃ ውስጥ ከሚያገለግሉ አባላት አገልግሎትን ወይም ዲስፕሊንን በተመለከተ የሚቀርብ አቤቱታ
- አንድ የመንግስት ሰራተኛ በአሰሪው መ/ቤት ላይ አገልግሎቱን በተመለከተ የሚያቀርበው አቤቱታ (አቤቱታው ከአዋጅ፣ ከመንግስት የአገልግሎት ደንብ ወይም ከሕብረት ስምምነት ድንጋጌዎች ጋር የሚቃረን ተግባርን የሚመለከት ካልሆነ በስተቀር)

## ማወቅ የሚያስፈልጉ ጠቃሚ ነገሮች

- ወደ የሕዝብ አቤቱታ ሰሚ ተቋም ከመምጣትዎ በፊት፣ ለሚመለከተው አካል ጥያቄዎትን አቅርበው መልስ መጠየቅ አስፈላጊ ነው (አስፈላጊ ሂደቶችን ማለፍ)
- አቤቱታ ለማቅረብ ምንም ዓይነት ክፍያ የማይጠየቅ ሲሆን በጠበቃ መወከልም አያስፈልግዎትም
- የአቤቱታ አቅራቢው ማንነት ያልተገለጸበት አቤቱታ መቅረብ የለበትም
- አቤቱታው በውጭ ሃገር ቋንቋ ማቅረብ ይቻላል
- ለአካል ጉዳተኞች አስፈላጊው ድጋፍ ይቀርባል

## የአቤቱታ ምርመራ ሒደት

**አቤቱታን መቀበል**

ንውታቱቤአ ምቋተ ሚሰ ታቱቤአ ብዝሕየ
?ውለአ ንጣልስ ርመርመመየ

**አቤቱታን የመመርመር ስልጣን እንደሌለው ለአቤቱታ አቅራቢው ማሳወቅ**

(ለምሳሌ፣ አቤቱታው ለየሕዝብ አቤቱታ ሰሚ ተቋም ሊቀርብበት የማይቻል አካል፤ ቀጥተኛ ጉዳት የማያስከትል፤ ጉዳዩ በፍ/ቤት በመታየት ላይ ከሆነ)

**ወደ ግልግል መምራት**

**አቤቱታን መመርመር**

- የአቤቱታ አቅራቢውን ዝርዝር መረጃዎች ማጣራት
- በአቤቱታው ላየ የእውነታና የሕግ ምርመራ ማድረግ
- አቤቱታ የቀረበበት አካል ምላሹን እንዲሰጥ ማነጋገር

የሕዝብ አቤቱታ ሰሚ ተቋም አቤቱታውን በምርመራ ሒደት ውስጥ ሊያግዝ ከሚችል ማንኛውም ሰው ወይም አካል መረጃና ሰነዶችን ሊጠይቅ ይችላል የአቤቱታ ምርመራ በስነ-ስርዓት ወይም በማስረጃ ሕግ ድንጋጌዎች መሰረት አይመራም።

**ምርመራውን ያለ ውሳኔ ማጠናቀቅ**

(ለምሳሌ፡ የአቤቱታው ጉዳይ ከተሻሻለ፤ አቤቱታ አቅራቢው አቤቱታውን ከሳበ፤ የሕዝብ አቤቱታ ሰሚ ተቋም አቤቱታውን የመመርመር ስልጣን እንደሌለው  ከተረጋገጠ)

**ውሳኔ**

**አቤቱታው ተገቢ ነው**

ለአቤቱታ አቅራቢው የሚሰጥ ማስታወቂያ

አቤቱታ የቀረበበት አካል ስለተፈጸመው ጥፋትና ስለሚስተካከልበት መንገድ ማስታወቂያ መስጠት

ችግሩ ከተስተካከለ በኋላ ክትትል ማድረግ

**አቤቱታው መሰረት የለውም**

ለአቤቱታ አቅራቢው እና አቤቱታ ለቀረበበት አካል የምርመራውን ግኝት በተመለከተ ማስታወቂያ መስጠት

## ሰብአዊ መብቶች

**ይህን ያውቁ ኖሯል?**

?

የሕዝብ አቤቱታ ሰሚ ተቋም በሃገረ እስራኤል ውስጥ ሰበዓዊ መብቶችን የሚመለከቱ ሕገ-መንግስታዊና ሕጋዊ ልማዶች የአቤቱታዎች ምርመራ የማዕዘን ድንጋይ እንደሆኑ ይገነዘባል።

በቅርብ አመታት ውስጥ፣ የሕዝብ አቤቱታ ሰሚ ተቋም መሰረታዊ መብቶቻቸው፣ ማለትም የእኩልነት መብት፣ የግል ነጻነት መብት፣ ሃሳብን የመግለጽ ነጻነትና በወንጀል የተከሰሱ ሰዎች መብታቸው በመጣሱ ለተጎዱ አቤቱታ አቅራቢዎች እገዛ አድርጓል።

## ሙስናን የሚያጋልጡ ሰዎች

**ይህን ያውቁ ኖሯል?**

?

ተቀጥሮ በሚሰራበት ተቋም ውስጥ የተፈጸመ የሙስና ተግባርን ያጋለጠ ሰራተኛን መብቶች ለማስጠበቅ የሕዝብ አቤቱታ ሰሚ ተቋም ገዥ ትእዛዞችን የመስጠት ስልጣን አለው።

በዚህ ረገድ፣ የሕዝብ አቤቱታ ሰሚ ተቋም የሰራተኛውን ስንብት ለመሻር ወይም ለልዩ ጉዳቶች ካሳ እንዲከፈል ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል።

## ማደራደር

**ይህን ያውቁ ኖሯል?**

?

በቅርብ አመታት ውስጥ፣ የሕዝብ አቤቱታ ሰሚ ተቋም ለድርድር ምቹ በሆኑ አቤቱታዎች ላይ የማደራደር ስራ ሲሰራ ቆይቷል። የማደራደር ጥቅም የምርመራው ሒደት ከአቤቱታው ተጨባጭ ሁኔታዎች ጋር እንዲጣጣሙ በማደረግ በአቤቱታ አቅራቢውና በመንግስታዊ አካል መካከል የተፈጠረ አለመግባባትን የመፍታት እድልን ይጨምራል።

የሕዝብ አቤቱታ ሰሚ ተቋም በድርድር ከሚፈታቸው ጉዳዮች መካከል የቅጥር ግንኙነቶች፣ አደጋና አካባቢ ብክለት (ለምሳሌ የድምፅ ብክለትና የአየር ብክለት) ማስወገድና የመንግስት ሃላፊዎች ተግባር ይገኙበታል።

## የሕዝብ አቤቱታ ሰሚ ተቋም አድራሻዎች



**ኻይፋ**
12 ሐሳን ሽኩሪ መንገድ፣ ሐዳር
ፖ.ሳ.ቁ. 4394, ኻይፋ 3104301
ስልክ፡ 04-8649748
ፋክስ፡ 04-8649744

**ናፅራት**
85 ጳውሎስ ሐሺሺ መንገድ፣ ሐመርካዝ ሐላቫን
ፖ.ሳ.ቁ. 50400, ናፅራት 1616202
ስልክ፡ 04-6455050
ፋክስ፡ 04-6455040
nazeret@mevaker.gov.il

**ተል አቪቭ - ያፎ**
19 ሐአርባዓ መንገድ (13ኛ ፎቅ)
ሚግዳል ሐቲኾን
ፖ.ሳ.ቁ. 7024
ተል አቪቭ - ያፎ 6107001
ስልክ፡ 03-6843555
ፋክስ፡ 03-6851512

**ኢየሩሳሌም**
2 መቫከር ሐመዲና መንገድ
ኪርያት ሐለኦም፣
ፖ.ሳ.ቁ. 1081

**ሎድ**
1 ሐጺዮኑት ጎዳና፣ ሚግዳል ከይሳር
ፖ.ሳ.ቁ. 727, ሎድ
ስልክ፡08-9465566
ፋክስ፡ 08-9465567
lod@mevaker.gov.il

**በኤር ሸባዕ**
8B ሐኔሪየታ ሶልድ መንገድ፣
ራስኮ ሲቲ ሕንጻ፣ ፖ.ሳ.ቁ. 599፣ ቢ
ስልክ፡ 08-6232777
ፋክስ፡ Fax 08-6234343
beersheva@mevaker.gov.il

ኮዱን ለሃገሪቱ ተቆጣጣሪ ድረ ገጽ ስካን ያድርጉ

### ከየሕዝብ አቤቱታ ሰሚ ተቋም ጋር ግንኙነት ማድረጊያ መንገዶች

**በኦንላይን ቅጽ** www.mevaker.gov.il
**በኢሜይል** ombudsman@mevaker.gov.il
**በፋክስ** 02-6665204
**በመደበኛ መልእክት መላኪያ** 2 Mevaker Hamedina Street, Kiryat Haleom, POB 1081, Jerusalem 9101001
**በፌስቡክ** Office of the State Comptroller and Ombudsman
**በየሕዝብ አቤቱታ ሰሚ ተቋም ቢሮዎች** በአካል ወይም በደብዳቤ ለዚሁ በተዘጋጀ ሳጥን ውስጥ በማስገባት

ይህ በራሪ ወረቀት የያዘው አጠቃላይ መረጃን እንጂ አስገዳጅ ጽሑፍ አይደለም። የአቤቱታዎችን ምርምራና የሕዝብ አቤቱታ ሰሚ ተቋም ስልጣኖችን በተመለከተ ሙሉና አስገዳጅ ድንጋጌዎች በሃገሪቱ የቁጥጥር ሕግ  5718-1958 [የተጠናቀረ እትም] ውስጥ በዝርዝር ቀርቧል።